HUMAN RIGHTS WATCH

# “የምንሰራውን ነገር ሁሉ ያውቃሉ”

## በቴሌኮም እና ኢንተርኔት የሚደረግ ክትትል

Copyright © 2014 Human Rights Watch
All rights reserved.
Printed in the United States of America
ISBN: 978-1-62313-1159
Cover design by Rafael Jimenez

Human Rights Watch defends the rights of people worldwide. We scrupulously investigate abuses, expose the facts widely, and pressure those with power to respect rights and secure justice. Human Rights Watch is an independent, international organization that works as part of a vibrant movement to uphold human dignity and advance the cause of human rights for all.

Human Rights Watch is an international organization with staff in more than 40 countries, and offices in Amsterdam, Beirut, Berlin, Brussels, Chicago, Geneva, Goma, Johannesburg, London, Los Angeles, Moscow, Nairobi, New York, Paris, San Francisco, Sydney, Tokyo, Toronto, Tunis, Washington DC, and Zurich.

For more information, please visit our website: http://www.hrw.org

# የሪፖርቱ ዋና ዋና ነጥቦች

> አንድ ቀን አሰሩኝ እና ሁሉንም ነገር አሳዩኝ፡፡ ሁሉንም የስልክ ልውውጦቼን ዝርዝር ካሳዩኝ በኋላ ከወንድሜ ጋር ያደረኩትን የስልክ ንግግር አሰሙኝ፤ ያሰሩኝ በስልክ ስለፖለቲካ ስላወራን ብቻ ነው፤ ለመጀመሪያ ጊዜ የያዝኩት የራሴ ስልክ ነበርና ከዚያ በኋላ በነጻነት ማውራት የምችል መስሎኝ ነበር፡፡
>
> አሁን ኬንያ በስደት ላይ የሚገኝ የኦሮሞ ተቃዋሚ ፓርቲ የቀድሞ አባል፤ ሜይ 2013

እ.ኤ.አ ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ የኢትዮጵያ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አቅም በአስገራሚ ፍጥነት አድጓል፡፡ ነገርግን አሁንም ኢትዮጵያ በአፍሪካ ከሚገኙ በርካታ ሃገራት ወደ ኋላ ቀርታለች፤ የሞባይል ስልክ ሽፋን እያደገ ሲሆን ኢሜይል እና ሌሎች የማህበራዊ ድረ-ገጾችን አገልግሎት ማግኘት መቻሉም በተለይ በከተሞች የሚኖሩ ወጣት ኢትዮጵያዊያን እርስ በእርስ እንዲገናኙ እና አስተያየቶቻቸውን እና ሃሳባቸውን እንዲለዋወጡ እድሉን ፈጥሯል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት የኢንተርኔት እና ሌሎች ኮምዩኒኬሽን ቴክኖሎጂዎችን መስፋፋት ጠቃሚ እድሎች እንደሆኑ ሊቆጥራቸው ይገባል፡፡ የቴሌኮምዩኒኬሽን ዘርፉን እድገት ማበረታታት ሃገሪቱን ለማዘመን እና ትልቅ ተስፋ የተጣለበትን የኢኮኖሚ እድገት እቅድ ለማሳካት ወሳኝ ነው፡፡

ነገር ግን ጎሳን መሰረት ያደረጉ ፓርቲዎች ጥምረት የሆነው እና ከ20 ዓመታት በላይ በስልጣን ላይ የሚገኘው ገዥው የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) ሃሳብን የመግለጽ ነጻነትን፣ የመደራጀት እና በሰላማዊ መንገድ የመሰብሰብ መብቶችን እጅግ በከፍተኛ ሁኔታ መገደቡን ቀጥሎበታል፡፡ አፋኝ የሆኑ ህጎችን በመጠቀም የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶችን እና ነፃ መገናኛ ብዙሃንን አጥፍቷል፤ እንዲሁም ፖለቲካዊ ተጽእኖ ያለባቸው ክሶችን በመመስረት ግለሰቦችን ያጠቃል፡፡ የኦሮሞ ብሄር ህዝብ በተለይ የዚህ ጥቃት ዓይነተኛ ተጎጂ ነው። ገዢው ፓርቲ በኦሮሞ ህዝብ ላይ ለሚያካሂደው ዘርፈ ብዙ ጭቆና የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ)በኦሮሚያ ክልል የሚያካሂደውን አነስተኛ የትጥቅ ትግል በምክንያትነት የሚያቀርብ ሲሆን ግንቦት ሰባትን ጨምሮ ከሌሎች የታገዱ ቡድኖች ጋር ግንኙነት መፍጠርም ለአፈናው መባባስ በምክንያትነት ይቀርባል።

በመሆኑም ኢትዮጵያዊያን ቴክኖሎጂን በመጠቀም ግንኙነት የማድረግ፣ ሃሳባቸውን የመግለጽ እንዲሁም የመደራጀት ችሎታቸው ከሚያበረክተው ማህበራዊ ጥቅም ይልቅ በሕዝቡ ላይ ያለውን ቁጥጥር ለማስቀጠል ስፋት ባለው የክትትል እና የስለላ ስራ ላይ ለሚተማመነው ገዢው ፓርቲ እንደ ፖለቲካ ስጋት ምንጭ የሚታይ ሆኗል።

የኢትዮጵያ መንግስት በኢንተርኔት እና ሞባይል ቴክኖሎጂዎች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር የሚያደርግ ሲሆን ይህም አገልግሎቱ ለምን ጥቅም እንደዋለ ለመከታተል እና የሚተላለፈውን የመረጃ አይነት እና አገልግሎት ለመገደብ አስችሎታል፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ከሌሎች የአፍረካ ሃገራት በተለየ መልኩ ኢትዮ-ቴሌኮም በተሰኘው መንግስታዊው የቴሌኮም አገልግሎት አቅራቢ አማካኝነት በፍጥነት እያደገ ያለውን የቴሌኮምዩኑኬሽን ዘርፍ ሙሉ በሙሉ በብቸኝነት ይቆጣጠራል። ይህ የመንግስት ክትትል የማድረግ አቅም ባልተገባ ሁኔታ ጥቅም ላይ መዋል አለመዋሉን የሚከታተል ገለልተኛ የህግ አውጪ እና ህግ ተርጓሚ አካል በኢትዮጵያ ስለሌለ መንግስት ዘርፉን በብቸኝነት በመቆጣጠር ያለምንም የበላይ ቁጥጥር መረጃ የማግኘት መንገድን ለመገደብ እና ሃሳብን የመግለጽ እና የመደራጀት ነጻነቶችን በብቃት ማፈን አስችሎታል፡፡

በአለም ዙሪያ የሚገኙ ሁሉም መንግስታት ክትትል/ስለላ/ ያደርጋሉ፤ሆኖም በአብዛኞቹ ሃገራት ቢያንስ ግለሰባዊ እና ሌሎች መብቶች እንዳይጣሱ የህግ አውጭ እና ህግ ተርጓሚ አካላት ቁጥጥር ማድረግ የሚችሉበት አሰራር አለ፡፡ በኢትዮጵያ እንዲህ አይነቱ የአሰራር ሂደት የለም፡፡ በርካታ ኢትዮጵያዊያን መንግስት ፍጹም የሆነ ክትትል የማድረግ አቅም እንዳለው ስለሚያስቡ ራሳቸውን በከፍተኛ ሁኔታ ሳንሱር የሚያደርጉ ሲሆን ይህም ኢትዮጵያዊያን በቴሌኮም ኔትዎርኮች ላይ በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ በሚያካሂዱት ውይይት ሃሳባቸውን በግልጽ ከመሰንዘር እንዲቆጠቡ በማድረግ መንግስት በተጨባጭ ማድረግ ከሚችለው በላይ ቁጥጥሩ የከፋ ተጽእኖ እንዲኖረው አድርጓል።

ይህ ሪፖርት እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 2012 እስከ ፌብሯሪ 2014 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በተደረገ ጥናት መሰርት የተዘጋጀ ሲሆን በ11 ሃገራት ከሚገኙ ከ100 በላይ ሰዎች ጋር የተደረጉ ቃለ-መጠይቆችን አካቷል፡፡የኢትዮጵያ መንግስት የግለሰባዊ መብትን፣ ሃሳብን የመግለጽ ነጻነትን፣መረጃ የማግኘትን እንዲሁም ሌሎች መብቶችን ለመገደብ በቴሌኮምዩኒኬሽን መዋቅሩ ላይ ያለውን ቁጥጥር  እንዴት እንደሚጠቀም የሚያሳዩ መረጃዎችን ይዘረዝራል፡፡ እነዚህ መብቶች በዓለምዓቀፍ ህግ የተደነገጉ ሲሆን መንግስትም በኢትዮጵያ ህገመንግስት የተካተቱ መሆናቸውን በተደጋጋሚ ይገልጻል፡፡ በተግባር ያለው ሁኔታ የሚያሳየው ግን የትኛውንም ዓይነት ሕጋዊ ጥበቃ ያለምንም ገደብ የሚጥሱት የመንግስት ባለስልጣናት በሚፈጽሟቸው ተግባራትና በእንከን በተሞሉ ሕጎች አማካኝነት አፈጻጸማቸው እንደሚደናቀፍ ነው።

የተቀዋሚ ፓርቲዎች ድረ-ገጾች፣ የነጻ መገናኛ ብዙሃን ድረ-ገጾች፣ ብሎጎች እና በርካታ የዓለምዓቀፍ መገናኛ ብዙሃን ስርጭቶች በመንግስት ተቆጣጣሪ አካላት በመደበኛነት ይታገዳሉ፡፡ የሬዲዮ እና ቴሌቪዥን ስርጭቶች ይገደባሉ፡፡ ብሎገሮች እና የፌስቡክ ተጠቃሚዎች በኢንተርኔት በሚያሰራጩት ጽሁፍ የሚያስተላልፉትን መልዕክት (ሃሳብ) ለማለሳለስ ፈቃደኛ ካልሆኑ ማስፈራሪያና የእስር ዛቻ ይደርስባቸዋል። መልዕክቱ ቀላል ነው፤ በመንግስት ላይ ልትሰነዝር የምትችለውን ትችት በተመለከተ ራስህን ገድብ ወይንም እኛ እንገድብሃለን፤ ልትታሰርም ትችላለህ የሚል፡፡

ከቴሌኮም እና ኢንተርኔት ምንጮች የሚገኙ መረጃዎች በጸረ-መንግስት እንቅስቃሴ ተወንጅለው በሚታሰሩ ኢትዮጵያዊያን ላይ በመደበኛነት ጥቅም ላይ ይውላሉ። በምርመራ ወቅት ፖሊስ ለተጠርጣሪዎች የተለዋወጧቸውን የስልክ ጥሪዎች  ዝርዝር በማሳየት ስለ ደዋዮቹ ማንነት ይጠይቃል፤ በተለይ ደግሞ ከውጭ ሃገር የደወሉ ሰዎችን ማንነት ያጣራል።ከጓደኞች እና የቤተሰብ አባላት ጋር የተደረጉ የስልክ ውይይቶችን ተጠርጥረው የተያዙ ሰዎች እንዲያዳምጡ ያደርጋሉ። መረጃው ያለምንም የፍርድቤት ትእዛዝ በተከታታይ ይወሰዳል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ የኤሌክትሮኒክ “ማስረጃዎች” ተጠርጣሪዎች የእምነት ቃል ወይም መረጃ እንዲሰጡ ለማስገደድ የሚውሉ ሲሆን አንዳንድ የተቀዱ/የተጠለፉ ኢሜይሎች እና የተቀረጹ የስልክ ውይይቶች በአፋኙ የጸረ-ሽብር ሕግ መሰረት በሚቀርቡ ክሶች ላይ ለፍርድ ቤት በማስረጃነት እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡

መንግስት በቴሌኮም እና ኢንተርኔት ላይ ያለውን ብቸኛ ባለቤትነት ህጋዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎችን ለማገድ ይጠቀምበታል፡፡ ሰላማዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች በሚደረጉበት ጊዜ የስልክ ኔትወርኮች ይዘጋሉ፡፡ በውጭ ሀገራት የሚኖሩ አንዳንድ ታዋቂ  ኢትዮጵያዊያንም  የኦን ላይን እንቅስቃሴን በድብቅ ለመከታተል በሚያስችሉ እጅግ በተራቀቁ የስለላ ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም የይለፍ ቃላቸውን (ፓስወርዳቸውን) እና በኮምፒውተራቸው ውስጥ የተቀመጠ መረጃን ለመስረቅ ኢላማ ተደርገዋል።

የሞባይል አገልግሎት ሽፋን እና የኢንተርኔት አገልግሎት እጅግ ውስን በሆነበት በተለይ በገጠሩ የኢትዮጵያ ክፍል ራስን ሳንሱር ማድረግ የተለመደ ሆኗል፡፡ ዋናው የመንግስት የመቆጣጠሪያ መንገድ በጣም ሰፊ የሆነው የመረጃ አቀባዮች መረቡ እና እስከታች የማህበረሰብ ስርዓት ድረስ የተዘረጋው የክትትል መንገዱ ነው፡፡ ይህም አብዛኞቹ በገጠር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የሞባይል ስልኮችን እና ሌሎች የቴሌኮምዩኒኬሽን ቴክኖሎጂዎችን እንደ ተጨማሪ  የመቆጣጠሪያ መሳሪያ አድርገው እንዲያዩ አድርጓቸዋል። በዚህም ምክንያት ሰዎች መንግስት በግል ሕይታቸው ውስጥ ጣልቃ ከመግባቱ ጋር ተያይዞ ያላቸው የኖረ ፍራቻ ወደ ሞባይል አጠቃቀማቸውም በመዛመቱ  በስልክ እና በኢሜይል በሚያደርጓቸው ግንኙነቶች ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ራሳቸውን ሳንሱር ያደርጋሉ። ቢያንስ በአሁኑ ወቅት ሕዝቡ መንግስት በስልክ ግንኙነቶች ላይ ያደርጋል ብሎ የሚያምነው ክትትል መንግስት በተጨባጭ እያደረገ ካለው ጋር ሲነጻጸር እጅግ የሰፋ ነው።

ኢትዮጵያ በዓለም ላይ በጣም አሉ የተባሉ የተራቀቁ የመከታተያ ቴክኖሎጂዎች አሏት፤ ሆንም ግን ክትትል የማድረጊያ ቴክኖሎጂዎችን የምትጠቀምበት መጠን በአቅም ምክንያት እና በቁልፍ የሚኒስቴር መስሪያቤቶች ላይ ሙሉ እምነት ለማሳደር ካለመቻል ጋር በተያያዘ ምክንያት ለጊዜው ውሱን ነው። ሁኔታው ለጊዜው እንደዚህ ቢሆንም  ኢትዮጵያውያን መንግስታቸውን ለመፈተሽና ጥያቄም ለማቅረብ ያላቸው ስር የሰደደ ፍራቻና መንግስት እጅግ የሰፋ የስለላና የክትትል ስራ ይሰራል ብለው ማመናቸው ግን ስለላና ክትትሉ ከሚያደርሰው እኩል ጉዳት አለው። ነጻ አስተሳሰቦችን የሚያንጸባርቁ ድምጾች ታፍነዋል፤ሃሳብን በነጻ የመግለጽና የመናገር መብቶች ተገድበዋል። የሂዩማን ራይትስ ዎች ጥናት እንደሚያሳየው ይህ ገና የመጀሪያው ብቻ ይሆናል። የመንግስት የሰው ሃይል አቅም ሲጠናከር ኢትዮጵያውያን ለተጠናከረ የስልክ እና የኢሜይል ክትትልና ስለላ መዳረጋቸው የማይቀር ነው።

የወንጀል እንቅስቃሴዎችን፣ ሙስናን እና ሽብርተኝነትን ለመከላከል የመልዕክት ልውውጦችን ማየት እና መከታተል ህጋዊ የአሰራር መንገድ ቢኖረውም ኢትዮጵያ ውስጥ ግን እንዲህ አይነቱን ተግባር የሚመለከት፣ሕግ ከሚፈቅደው ውጭ እንደማይከናወን እና  የመልዕክት ልውውጦች እና የተሰበሰቡ መረጃዎች እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ የሚደነግግ አሰራር

እና መመርያ የለም። በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በፍጥነት እያደገ የመጣው የኢንፎርሜሽን እና ኮምዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ በአግባቡ እና ከዚህ በፊት ከነበረው እጅግ በተለየ መልኩ ሰዎች እንዲገናኙ አዲስ እድል ፈጥሯል፤ ፖለቲካዊ ውይይቶችን ለማካሄድ የሚያስችል ሁኔታን እና መረጃ የማግኘት መንገድን ጨምሯል፡፡ ነገርግን በርካታ ኢትዮጵያዊያን እነዚህን እድሎች ለመጠቀም አልታደሉም፡፡ ይልቁንም የኢንፎርሜሽን እና ኮምዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ህዝብን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሮ ለማቆየት መንግስት የሚፈልገው ሌላ መንገድ ሆኖ ጥቅም ላይ ውሏል፤ ይህም ሃሳብን የመግለጽ ነጻነት እና የመደራጀት መብቶችን በማፈን፣ ግለሰባዊ መብቶችን በመግፈፍ፣ የመረጃ ተደራሽነትን በመገደብ ብሎም የተለዩ ሃሳቦች እንዳይንሸራሸሩ እና ትርጉም ያለው ውይይት እና ክርክር እንዳይደረግባቸው ያደርጋል።

ክትትል እና ብርበራ ለማድረግ የፍርድቤት ትእዛዝ የሚያስፈልግ ቢሆንም በተግባር ግን አይፈጸምም፡፡ የመልዕክት ልውውጦችን በመጥለፍ የሚገኙ መረጃዎች የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን እና በገዢው ፓርቲ ላይ ትችት የሚሰነዝሩ ሰዎችን ለማጥቃት መሳሪያ ሆነዋል። የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት፣ ጋዜጠኞች፣ እና ወጣት እና የተማሩ የኦሮሞ ብሔር አባላት በዋናነት ትኩረት ከሚደረግባቸው ውስጥ ይካተታሉ፡፡

ክትትል ማድረግ የሚያስችለውን የመሰረተ ልማት አቅም የኢትዮጵያ መንግስት ብቻውን ያደራጀው አይደለም፤ በኢንተርኔት እና ቴሌኮም ሴክተር መዋዕለ ነዋያቸውን ባፈሰሱ የቻይና እና በአውሮፓ የሚገኙ ኩባንያዎች እርዳታም ጭምር ነው። እነዚህ የውጭ ኩባንያዎች ዘርፉን ለማዘመን የቴክኖሎጂ ውጤቶችን፣ አገልግሎቶችን እና የሙያ እገዛ አቅርበዋል፡፡

ኢትዮጵያ ግለሰባዊ መብቶች ለመጠበቅ እና ለማስከበር በወጡ ዓለም ዓቀፍ ድንጋጌዎች መሰረት አግባብነት ያለው ህጋዊ ማዕቀፍ ከማውጣት በተጨማሪ የህግ ማእቀፉን በትክክል ስራ ላይ ማዋል አለባት፡፡ የክትትል ማድረጊያ ቴክኖሎጂዎችን፣ ሶፍትዌሮችን ወይም አገልግሎቶችን የሚያቀርቡ ኩባንያዎች እነዚህ ምርቶች ለተገቢው የህግ የማስከበር አገልግሎት እንጂ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን፣ ጋዜጠኞችን፣ብሎገሮችን እና ሌሎችንም የማፈኛ መሳሪያ ሆነው ጥቅም ላይ እንዳይውሉ የሚያረጋግጥ ፖሊሲ መቅረጽ አለባቸው፡፡

# የማሻሻያ ነጥቦች

## ለኢትዮጵያ መንግስት

- በኢትዮጵያም ላይ ተፈጻሚ በሆኑ የዓለም ዓቀፍ ህግ ድንጋጌዎች በተረጋገጠው መሰረት ግለሰባዊ መብቶች እንዳይነኩ እና በዘፈቀደ ለክትትል፣ ለብሔራዊ ደህንነት እና ለሕግ አስፈጻሚ ሃይሎች ስራ ጥቅም እንዳይውሉ ህጋዊ ጥበቃ ማድረግ፡፡ ክትትል ማድረግ የሚቻለው በህግ በተደነገገ መንገድ ብቻ እንዲሆን ማድረግ፤ ይህም አስፈላጊ እና ከታቀደው ህጋዊ ዓላማ ጋር የተመጣጠነ መሆኑን ማረጋገጥ እንዲሁም በህግ ተርጓሚው እና በህግ አውጭው አካል ቁጥጥር እንዲደረግበት ማድረግ።
- የክትትል ስራዎች ዓይነት፣ ስፋት እና የሚወስዱት ጊዜ፣ ክትትሉ እንዲካሄድ ለመወሰን መሟላት ያለባቸው መሰረታዊ ሁኔታዎች፣ ክትትሉን ለማስፈጸም፣ ለመተግበር እና ለመቆጣጠር ስልጣን ያላቸው ባልስልጣናት የትኞቹ እንደሆኑ የሚያሳይ ሕጋዊ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረግ።
- ከፍርድ ቤት ማዘዣ ውጪ ከኢሜይል ወይንም ስልክ በመጥለፍ የተገኙ መረጃዎች እና የተቀረጹ ስልኮች ፍርድቤት በማስረጃነት ተቀባይነት የማይኖራቸው መሆኑን ማረጋገጥ፤ የተጠለፉ መረጃዎች በማስረጃነት ፍርድቤት እንዲቀርቡ የሚደነግጉ ህጎች መረጃዎቹን ለማግኘት የፍርድቤት ትእዛዝ አስፈላጊ መሆኑን በሚገልጽ መልኩ ማሻሻል፤ ይህም የወንጀለኛ መቅጫ ህጉን፣ የቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀል አዋጅ፣ የህገወጥ ገንዘብ ዝውውርን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መደገፍ ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣውን ህግ ያካተተ እንዲሆን።
- የተደወሉ ስልኮች ማጠራቀሚያ መዝገቦች እና ሌሎች የመረጃ ቋቶች የህግ ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል፤ እንደዚህ አይነት መረጃዎች ያለፍርድቤት ትእዛዝ እና የበላይ ቁጥጥር በፖሊስ፣ በደህንነት ወይም በስለላ ተቋም እንዳይሰበሰቡ ወይም እንዳይወሰዱ እና ያለአግባብ እና ያለፈቃድ ጥቅም ላይ እዳይውሉ ወይም መረጃው ይፋ እንዳይሆን ማድረግ።
- በጸረ-ሽብር አዋጁ እና በብሄራዊ የመረጃ እና ደህንነት ኤጀንሲ አዋጅ ምርመራ ወይም ክትትል ከመደረጉ በፊት የፍርድቤት ትእዛዝ ማውጣት አስፈላጊ እንደሆነ የሚገልጹትን ድንጋጌዎች ስራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፡፡ በዓለም ዓቀፍ መመዘኛዎች መስፈርት መሰረት ስልጣን ካለው፣ ነጻ ፍርድቤት ትዕዛዝ እስካልቀረበ ድረስ ኢትዮ-ቴሌኮም የተደወሉ ስልኮች ማጠራቀሚያ መዝገቦቹን እና ሌሎች የመረጃ ቋቶቹን ለደህንነት አካላት ክፍት ማድረግ የለበትም፡፡ በመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ወይም በብሄራዊ የመረጃ እና ደህንነት አገልግሎት የሚሰበሰብ ማንኛውም መረጃ ወይም የሚካሄድ ምርመራ ቅድሚያ የፍርድቤት ይሁንታን ማግኘት አለበት፡፡
- የታገዱ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የመገናኛ ብዙሃን እና የብሎገሮችን ድረ -ገፆች በአስቸኳይ መልቀቅ፤ ወደፊትም ዌብሳይቶች እንደማይታገዱ ማረጋገጫ መስጠት።
- የሬድዮ እና የቴሌቪዥን ስርጭቶችን የማፈን ተግባር በአስቸኳይ እንዲቆም እና ወደፊት ም እንደማይፈጸም ማረጋገጥ።
- ሃሳብን በነጻ የመግለጽ መብታቸውን በመጠቀም በኢንተርኔት አማካይነት በማህበራዊ ድረ ገጾች እና በብሎጎች ሃሳቦቻቸውን የሚገልጹ ሰዎች ላይ የሚፈጸሙ የማስፈራራትና የማዋከብ ተግባራት እንዲቆሙ።
- ህጋዊ ባልሆነ መንገድ በተጠለፈ ወይም በተገኘ መረጃ መሰረት ግለሰቦችን በዘፈቀደ ያሰሩ ወይም ባገቱ አሊያም ባሰቃዩ ሃላፊዎች ላይ ያለምንም የደረጃ እና የስልጣን ልዩነት በአግባቡ የዲሲፕሊን እርምጃ መውሰድ አሊያም ክስ መመስረት።
- መንግስት ምርመራ የማድረግ ስልጣን አጠቃቀሙን በተመለከተ በየዓመቱ ሪፖርት እንዲያወጣ። ይህ ሪፖርት ከኢትዮ ቴሌኮም፣ከኢንተርኔት ካፌዎች ወይም ከሌሎች የስልክ ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት አቅራቢዎች ምን ያህል ቁጥር ያለው መረጃ እንደተጠየቀ እና የተገኘውን መረጃ ያካተተ መሆን አለበት፤ ምን ያህል ቁጥር ያለው በቀጥታ የሚደረግ የስልክ ውይይት እንዲጠለፍ ወይም እንዲቀረጽ ጥያቄ እንደቀረበ እንዲሁም ምን ያህል ሰዎች ወይንም አካውንቶች በዚህ ጥያቄ መሰረት እንደተፈለጉም እንዲያካትት ማድረግ።
- በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች ወቅት ኔትዎርኮችን ለመዝጋት እና ግንኙነትን ለመጥለፍ የሚያስችለው ስልጣን ያለአግባብ ጥቅም ላይ እንዳይውል ለመከላከል እንዲቻል ሀሳብን በነጻ ለመግለጽ እና ለግለሰባዊ መብቶች ህጋዊ ጥበቃ ማድረግ።

- የጸረ-ሽብርተኝነት አዋጅ፣ የብሄራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት አዋጅ፣ የቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀል አዋጅ እና ህገወጥ የገንዘብ ዝውውርን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መደገፍን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጡትን ህጎች ጨምሮ ግለሰባዊ መብትን፣ መረጃ የማግኘት መብት እና ሃሳብን የመግለጽ መብትን፣ የመደራጀት፣ የመንቀሳቀስ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብቶችን የሚጥሱ ህጎችን ከዓለም ዓቀፍ ህግጋት ጋር በሚጣጣም መልኩ ማስተካከል ወይም ማሻሻል። ማሻሻያዎቹ የሚከተሉትን አንቀጾች መጨመር አለባቸው፡
    - የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ፤ አንቀጽ 23(1) እና (2) (በተዘዋዋሪ የተገኙ ወይንም የስሚ ስሚ ማስረጃዎችን ይፋ አለማድረግን የሚመለከተው) እና የብሄራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት አዋጅ አንቀጽ 27 (የብሄራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት ለሚፈልገው መረጃ ትብብር የሚጠይቅበትን ሁኔታ የሚመለከተውን)፡፡ የኢትዮ ቴሌኮም እና የመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ሃላፊዎች ከብሄራዊ የመረጃ እና የደህንነት አገልግሎት ጋር መተባበር ያለባቸው የተጠቃሚን መረጃ ለማግኘት የፍርድቤት ማዘዣ ሲቀርብ ብቻ መሆን አለበት፡፡
    - የቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀል አዋጅ አንቀጽ 6(1) (በጸረ-ሽብርተኝነት ህጉ መሰረት የተጠቀሱ እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ መልዕክት ማሰራጨት ወንጀል መሆኑን ይደነግጋል) እና አንቀጽ 10(3)(ኢንተርኔትን በመጠቀም የስልክ ጥሪ አገልግሎት መስጠት ወንጀል መሆኑን ይደነግጋል)፡፡

## ኢትዮጵያን በማገልገል ላይ ለሚገኙ ዓለምዓቀፍ የቴክኖሎጂ እና ቴሌኮም ኩባንያዎች

- ሃሳብን የመግለጽ ነጻነት፣ መረጃ የማግኘት፣ የመሰብሰብ እና ግለሰባዊ መብቶች ላይ አደጋ ሊጋርጡ የሚችሉ የንግድ እንቅስቃሴዎችን መገምገም። ተዘጋጅተው የተቀመጡ መሳሪያዎች ለመንግስታት ሲሸጡ ህገወጥ ክትትልን ወይንም ሳንሱርን የበለጠ ለማቀላጠፍ ባልተገባ መልኩ ጥቅም ላይ የሚውሉበትን እድል ለመቀነስ ጥናት ማድረግ፡ ፡ ለህግ አስፈጻሚ፣ የመረጃ እና ደህንነት ኤጀንሲ ደንበኞች በልዩ መልኩ የሚሰሩ ምርቶች እና አገልግሎቶች ላይም ይህንኑ አደጋ በተመለከተ ጥናት እና ግምገማ ማድረግ።
- በጨረታ ወይንም የኮንትራት ድርድር ሂደት ላይ በተለይ ሁለት ጥቅም ያላቸው ህጋዊ የመጥለፊያ ወይም የመከታተያ ሶፍትዌሮች እና መሳሪያዎችን በተመለከተ ምርቶቹ እና አገልግሎቶቹ በመጨረሻ ለምን ጥቅም እንደሚውሉ እና የመጨረሻ ተጠቃሚዎቹን አካላት በተመለከተ መጠይቆችን ማድረግ እና ማጣራት።
- የሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ መመዘኛዎችን በንግድ ሂደት ስምምነት ውስጥ ማካተትን ጨምሮ በንግድ ስራዎች እና አዳዲስ ኮንትራቶች ላይ ምርቶችን ያለአግባብ የመጠቀም እድልን ለማስቀረት ስትራቴጂዎችን መቀረጽ፡፡ እንደዚህ አይነት ስትራቴጂዎች ከግሎባል ኔትወርክ ኢኒሽየቲቭ መርሆች እና የተባበሩት መንግስታት “መጠበቅ፣ ማክበር እና መፍትሔ መስጠት” ከሚለው የንግድ እና የሰብዓዊ መብቶች የአሰራር ማእቀፍ ጋር እንዲጣጣሙ ማድረግ።
- ምርቶች እና አገልግሎቶች ባልተገባ ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ የሚያግድ ፖሊሲ እና የአሰራር ስርዓቶችን መቅረጽ፤ ይህም በመጨረሻ ምን ጥቅም ላይ እንደሚውል ወይም የመጨረሻውን ተጠቃሚ አካል የሚገልጹ የውል ድንጋጌዎችን ማስፈርና፣ አንድ ድንጋጌ ሲጣስ ኩባንያው አገልግሎቱን ማቅረቡን እና የቴክኒክ ድጋፍ ወይም የማሻሻል ስራውን ማቆም እንዲያስችለው ሆኖ መቀረጽ፤ ማንኛውም ምርት እና አገልግሎት ላልተገባ ጥቅም ስለመዋል አለማዋሉ በየጊዜው መፈተሽ፤ እንዲሁም በንግድ ስራ ወቅት በሰብዓዊ መብቶች ላይ ሊደርስ የሚችል አደጋን ለመከላከል ተጨባጭ እርምጃዎች መውሰድ።
- ኩባንያው መንግስታት ለሳንሱር፣ ለህገወጥ ክትትል ማድረጊያ፣ ወይም ኔትወርኮችን ለመዝጋት የሚያቀርቡትን ጥያቄዎች ውድቅ ለማድረግ የሚያስችለው ሰብዓዊ መብቶችን የተመለከቱ ፖሊሲዎች እና የአሰራር ስርዓቶች እንዲኖሩት፣ከመጠን ያለፉ እና የሕግ ድጋፍ የሌላቸው ጥያቄዎች ከመንግስታት የሚቀርቡበትን እድል የሚቀንስ ወይም ጥያቄዎቹን ለመቃወም የሚያስችሉ የአሰራር ስርዓቶችን መዘርጋት።
- የሰብዓዊ መብቶች ፖሊሲዎችና እና አሰራሮቹ ምርቱን ገዝተው ድጋሚ በሚሸጡ፣ በአከፋፋዮች እና በሌሎች የንግድ አጋሮችም ላይ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ማድረግ።
- ግሎባል ኔትዎርክ ኢንሽየቲቭን የመሳሰሉ የባለብዙ ባለድርሻ አካላት ስብስቦችን መቀላቀልን ጨምሮ የኩባንያው አሰራር ከሰብዓዊ መብቶች መመዘኛዎች ጋር የተጣጣሙ መሆኑን ከሚከታተሉ ነጻ እና ግልጽ ሶስተኛ ወገኖች ጋር መተባበር።
- ክትትል የማድረጊያ እና የሳንሱር ህጎች ከዓለማቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ ደረጃ ጋር በተጣጣመ መልኩ ማሻሻያ እንዲደረግባቸው ቅስቀሳ ማድረግ።

- ከ2008 ዓ.ም. በፊት የተደረጉ ኮንትራቶች እና የንግድ ግንኙነቶችን መፈተሽ፤ እንዲሁም በእነዚህ ኮንትራቶች መሰረት በአሁኑ ወቅት የቀጠሉ ስራዎች የሚያደርሱትን ጉዳት ለማስቀም እና ለመከላከል በ2008 ዓ.ም. ከወጡት የግሎባል ኔትወርክ ኢኒሽየቲቭ እና የተባበሩት መንግስታት መርሆች ጋር የሚጣጣሙ ስትራቴጂዎችን መንደፍ፤ ኮንትራቶቹ ለእድሳት በሚቀርቡበት ወቅት የሰብዓዊ መብቶች ጥበቃዎችን በአዲሶቹ ስምምነቶች ውስጥ ማካተት።

## ለቻይና፣ ለጀርመን፣ ለኢጣልያ፣ ለዩናይትድ ኪንግደም እና ለሌሎችም መንግስታት

- ለሁለት አይነት ጥቅም ሊውሉ የሚችሉ እንደ ዲፕ ፓኬት ኢንስፔክሽን መሳሪያ እና የሌላ አካልን መረጃ ማግኘት የሚያስችሉ ሶፍትዌሮችን የመሳሰሉ ክትትል የማድረጊያ እና የሳንሱር ቴክኖሎጂዎች የተመለከቱ የውጭ ሽያጮችን ስርዓት መቆጣጠር፤ እንዲህ አይነት ኩባንያዎች በውጭ ሃገራት በሚሰሩበት ወቅት ለብሄራዊ ድንጋጌዎች ተገዢ በመሆን ማንኛውንም የሰብዓዊ መብቶችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን ሪፖርት እዲያደርጉ እና የመብት ጥሰቶችን ለማስቀም እና ከተፈጸሙም ለማስተካከል የሚያስችል ቅድመ እርምጃዎችን እንዲወስዱ የሚያደርግ ስርዓት መዘርጋት።
- የሰብአዊ መብቶች ለከፍተኛ አደጋ ሊጋለጡ በሚችሉባቸው የውጭ ሃገራት  የመከታተያ ሶፍትዌሮች፣ ቴክኖሎጂዎች ወይም አገልግሎቶችን የሚሸጡ ኩባንያዎች የሰብአዊ መብቶችን መመዘኛዎች ተከትለው የሚሰሩ መሆናቸውን የሚከታታል እንደ ኦምቡድስማን ያለ መንግስታዊ ተቋም ቁጥጥር ማድረግ የሚችልበትን አሰራር መዘርጋት፤ ይህ ስርዓት እነዚህ ኩባንያዎች ከኢትዮጵያ ጋር በሚያደርጉት የንግድ ግንኙነት ምክንያት ጉዳት ደርሶብናል የሚሉ ግለሰቦች፣ቡድኖች ወይም ተወካዮቻቸው አቤቱታ ማድረግ የሚችሉበትን ስርዓት የሚያመቻችና በአቤቱታዎቹ መነሻነት የሚሰጡ ውሳኔዎች በኩባንያዎቹ ላይ አስገዳጅ የሆነ ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው ማድረግ።
- በኢትዮጵያ ስራ ላይ የሚገኙ ካምፓኒዎች ከላይ የተጠቀሱ የማሻሻያ ነጥቦችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ እንደሚጠበቅ የኢትዮጵያ መንግስት እንዲያወቀው ማድረግ።

## ለዓለም ባንክ፣ለአፍሪካ ልማት ባንክ፣ እና ለሌሎች ለጋሽ ድርጅቶች

- ግለሰባዊ መብቶችን፣ ሃሳብን የመግለጽ ነጻነትን፣ የመደራጀት፣ የመንቀሳቀስ እና መረጃ የማግኘት መብቶችን ሳንሱር በማድረግ፣ ህገወጥ በሆነ ክትትል ወይንም ኔትዎርኮችን በመዝጋት ጨምሮ የመብት ጥሰቶችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ላለመደገፍ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ የቴሌኮምዩኒኬሽን ፕሮጀክቶች ላይ የሰብዓዊ መብቶች መመዘኛዎች ተፈጻሚ እንዲሆኑ የሚጠበቅባቸውን ጥረት ማድረግ።ይህም ፕሮጀክቶች ጸድቀው ተግባራዊ መሆን ከመጀመራቸው በፊት በሰብአዊ መብቶች ላይ የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ መገምገምና ይህንንም ፕሮጀክቶቹ እስኪጠናቀቁ ድረስ ባለው ጊዜ ሁሉ መቀጠል፣ አደጋዎችን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚወሰዱ እርምጃዎችን መለየት፣ እና በሶስተኛ ወገኖች ጭምር ሰፋ ያለ ቁጥጥር በፕሮጀክቶቹ ላይ ማድረግን የሚጨምር እንዲሆን፤ይህ ግዴታን የመወጣት መስፈርት በሁሉም የመንግስት እና የግል ዘርፍ ተወናዮች ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን እና ይህም እነዚህ ወገኖች በመብቶች ጥሰቶች አለመሳተፋቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል እንዲሆን።
- ሳንሱር፣ ህገወጥ ክትትል፣ እና ኔትዎርኮችን መዘጋትን በተመለከተ እንዲሁም የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ልማትን እንደሚጎዳ ለመንግስት ባለስልጣናት በይፋም ሆነ በግል በሚደረጉ ግንኙነቶች ወቅት ማንሳት።